# <u>ወንጀለኞች የሚጠየቁት በስራቸው እንጂ በያዙት ፓስፖርት አይደለም !!!!!</u>

የዉጭ ሀገር ዜግነት የያዙ በደርግ ጊዜ ዜጎችን ሲገድሉ ሲገርፉ የነበሩ አሜሪካን ሀገር ክስ ተመስርቶባቸው በማስረጃ አሜሪካን ወህኒ ወርደዋል።

በካናዳ ይኖሩ የነበሩ በሩዋንዳው የዘር ጭፍጨፋ የተሳተፉ ለፍርድ ቀርበዋል።

በ ናዚ ጀርመን ወንጀል የተሳተፉ የ አሜሪካን ዜግነት ያላቸው ዜግነታቸው ተገፈው ወንጀል ወደ ፈፀሙበት አገር ተመልሰዋል።

ዛሬ ጠቅላይ ምኒስትር ዐቢይ አህመድ የዉጭ ፓስፖርት ይዘው መገናኛ ብዙሀንን በመቆጣጠር ህዝብ በህዝብ ላይ በማነሳሳት ያሉትን አዉግዘው እርምጃ እንደሚወሰድ ተናግረዋል።

ከ ሜኔሶታ ጀምሮ የጎሣ ማነሳሳት ስራ በ ቪዲዮ ማስረጃ ያለበት የጃዋር መሀመድ OMN ወደ ሁለት ዐመት ገደማ አትነሳም ወይ ፊንፌኔ ያንተ አይደለም ወይ እያለ ቄሮን ሲያደራጅ ዝምታን የመረጠው የጠቅላይ ምኒስትሩ ኦዴፓ ተጠያቂ ነው።

በቅርቡ ኢሬቻ 150 ከ ሽመልስ አብዲሣ ጎን ቆሞ አዲስ አበባ መስቀል አደባባይ እንዲፎክር ያደረገው የጠቅላይ ምኒስትሩ ኦዴፓ ተጠያቂ ነው።

ጃዋር መሀመድ ኮንዶሚኒየም በመቀማት ስብሰባ በመበተን መንገድ በማዘጋት የትግል ስልቱ አድርጎ መስራቱ አሮጌ የትግል ስልት ተደርጎ ቢነገርም የሀገራችንን ህዝብ በማሸበር የአካል የህይወት ና የኢኮኖሚ ጉዳት በማድረሱ ኦዴፓ ተጠያቂ ነው።

ባለፉት ጥቂት ቀናቶች ብቻ አዲስ አበባ አካባቢ ኦዴፓ ና ኢዜማ የ ጠቅላይ ምኒስትር አጋሮች በዱላና ድንጋይ በቄሮዎች ተበትንዋል።

በተመሳሳይ ጥቅምት ሁለት በባለአደራው ምክርቤት የተጠራውን ህዝባዊ ሠልፍ የተከለከው ታከለ ኡማም ሆነ መከላከያ ስራቸውን እንዲሰሩ ስላልተፈለገ ነው።

መጪዉ ምርጫ እንከን የለሽ አለመሆኑን ጠቅላያችን ቢናገሩም ዕዉነቱ ህዝቡ ፈርቶ ቤቱ የሚቀመጥበት በቅርቡ ያየነው የ አፍጋኒስታን አይነት ምርጫ ለማድረግ መሆኑ ግልፅ ነው ።

ህዝብ ከምርጫ በፊት እንዳይሰበሰብ ተቃዋሚ ፓርቲዎች እንዳይነቃነቁ ባሉበት ሁኔታ ምርጫ ተዘጋጅቶ የሚያሸንፈው የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት አዛዥ የ 2019 ኖቤል ተሸላሚው የመደመር ፍልስፍና አባት ዐቢይ አህመድ የሚመሩት ኢህአዴግ ወይም ተዋህዶ ኢህአዴግ መሆኑን የማይቀበል ዐይንና ጆሮ የሌለው ብቻ ነው።